የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥረኛ ዓመት ቁጥር ፰
አዲስ አበባ–ጥቅምት ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፮

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

10th Year No. 8
ADDIS ABABA–28th October, 2003

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፫/፲፱፻፺፮ ዓ.ም.
የኢንቨስትመንት (ማሻሻያ) አዋጅ ..... ገጽ ፪ ሺ፬፻፴፪

CONTENTS

Proclamation No. 373/2003
Investment (Amendment) Proclamation .. Page 2432

አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፫/፲፱፻፺፮
የኢንቨስትመንት አዋጅን እንደገና ለመደንገግ የወጣውን
አዋጅ ቁጥር ፪፻፹/፲፱፻፺፬ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

ኢንቨስትመንት የሚመራበትን ሥርዓት ግልጽና ቀልጣፋ እንዲሆን ማድረግ በማስፈለጉ ፤

ለዚህም በሥራ ላይ ያለውን የኢንቨስትመንት ሕግ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ–መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት እንደሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢንቨስትመንት (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፫፻፸፫/፲፱፻፺፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· የስያሜ ለውጥ

በአዋጅ ቁጥር ፪፻፹/፲፱፻፺፬ መሠረት እንደገና የተቋቋመው የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ተብሎ ተሰይሟል ።

፫· ማሻሻያ

የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር ፪፻፹/፲፱፻፺፬ እንደሚከተለው ተሻሽሏል ።

፩) የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፰) እና (፱) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፰) እና (፱) ተተክተዋል ።

"፰. "ማስፋፋት ወይም ማሻሻል" ማለት የነባር ድርጅትን የሙሉ አቅም ምርት ወይም አገልግሎት ከጽ፭ ፕርሰንት በላይ በእሴት ማሳደግ ሲሆን ይህም በዓይነት ወይም በመጠን ወይም በሁለቱም መጨመርን የሚያጠቃልል ነው ።

PROCLAMATION NO. 375/2003
A PROCLAMATION TO AMEND THE INVESTMENT RE-ENACTMENT PROCLAMATION NO. 280/2002

WHEREAS, the system of administration of investment needs to be transparent and efficient;

WHEREAS, to this end, it has become necessary to amend the existing law on investments;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*
This Proclamation may be cited as the "Investment (Amendment) Proclamation No. 375/2003."

2. *Renaming*
The Ethiopian Investment Authority, which has been re-estabilshed under Proclamation No. 280/2002, is hereby renamed as the Ethiopian Investment Commission.

3. *Amendment*
The Investment Proclamation No. 280/2002, is hereby amended as follows:

1) Article 2 Sub-Articles (8) and (9) of the Proclamation are deleted and replaced by the following new Sub-Articles (8) and (9).

"8. "Expansion/upgrading" means increasing in value, by more than 25%, the full production of service capacity of an existing enterprise, be it in variety, volume, or both.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 3.40

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

"፱. "አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት" ማለት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን (ከዚህ በኋላ "ኮሚሽኑ") ወይም የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ሥልጣን የተሰጠው የክልል ኢንቨስትመንት አካል ነው።"

፪) በአዋጁ አንቀጽ ፪ ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲፬) ተጨምሯል ።

"፲፬. "የቴክኖሎጂ ሽግግር" ማለት ምርትን ለማምረት ወይም የአመራረት ሂደትን ተግባራዊ ለማድረግ ወይም ለማሻሻል ወይም አገልግሎት ለመስጠት የሚረዳ ሥርዓት ያለው ዕውቀት ማስተላለፍ ሲሆን የማኔጅመንትና የግብይት ሁኔታ ቴክኖሎጂንም ይጨምራል ፣ ሆኖም ዕቃዎችን ብቻ ለመሸጥ ወይም ለማከራየት የሚደረግን ግንኙነት አይሸፍንም።"

፫) በአዋጁ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሥር የሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ሐ) ተጨምሯል ።

"(ሐ) ከሰባ በላይ መንገደኞችን የመጫን አቅም ባለው ኤርክራፍት የሚካሄድ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት።"

፬) የአዋጁ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል ።

"፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ነባር ድርጅትን ገዝቶ ባለበት ሁኔታ ለማካሄድ ወይም የነባር ድርጅትን አክሲዮን ለመግዛት የሚፈልግ የውጭ ባለሀብት ጥያቄውን ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በማቅረብ የሚኒስቴሩን ፈቃድ ማግኘት አለበት።"

፭) በአዋጁ አንቀጽ ፲፪ ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተጨምሮ የቀድሞው ንዑስ አንቀጽ (፫) ንዑስ አንቀጽ (፬) ሆኗል ።

"፫. የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ማመልከቻ ሲቀርብለት ጉዳዩን አግባብ ካለው ሕግ አንፃር በመመርመር በሁለት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ፡

ሀ) ማመልከቻውን ከተቀበለው ተገቢውን ክፍያ በማስከፈል የአክሲዮን ዝውውሩን ይመዘግባል ወይም የንግድ ሥራ ፈቃዱን ይተካል ፣ ወይም

ለ) ማመልከቻውን ካልተቀበለው ያልተቀበለበትን ምክንያት ለባለሀብቱ በጽሁፍ ያሳውቃል"

፮) የአዋጁ አንቀጽ (፲፫) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፲፫ ፣ ፲፬ እና ፲፭ ተተክቷል ። በዚህም መሠረት ከ፲፬–፴፰ ያሉት የአዋጁ አንቀጾች እንደ ቅደም ተከተላቸው ከ፲፮–፵ ሆነው ተሰተካክለዋል ።

"፲፫. በአገር ውስጥ ባለሀብት ስለሚቀርብ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ጥያቄ

፩ ማንኛውም የአገር ውስጥ ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማግኘት ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ከሚከተሉት ሠነዶች ጋር ማቅረብ አለበት ፡

ሀ) ማመልከቻው የተፈረመው በወኪል ከሆነ የውክልና ሥልጣን ማረጋገጫ ሠነድ ፎቶ ኮፒ ፣

ለ) ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው በግለሰብ ከሆነ የባለሀብቱ የመታወቂያ ካርድ ፎቶ ኮፒ ፣ ወይም የሀገር ውስጥ ባለሀብትነት ሰርተፊኬት ፎቶ ኮፒ እና ሁለት የቅርብ ጊዜ ጉርድ ፎቶግራፎች ፣

"9. "Appropriate Investment Organ" means the Ethiopian Investment Commission, (hereinafter referred to as the "Commission"), or the executive organ of a region empowered to issue investment permits."

2) The following new Sub-Article (14) is added under Article 2 of the Proclamation.

"14. "Transfer of technology" means the transfer of systematic knowledge for the manufacture of a product, for the application of improvement of a process or for the rendering of a service, including management and marketing technologies, but shall not extend to transactions involving the mere sale or lease of goods."

3) The following new item (c) is added under Article 5 Sub-Article (1) of the Proclamation.

"c. Air transport services using aircraft with a seating capacity of more than 20 passengers."

4) Article 12 Sub-Article (2) of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (2).

"2. Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, a foreign investor intending to buy an existing enterprise in order to operate it as it stands or to buy shares of an existing enterprise shall obtain prior approval from the Ministry of Trade and Industry,"

5) The following new Sub-Article (3) is added under Article 12 of the Proclamation and the previous Sub-Article (3) is renumbered as Sub-Article (4).

"3. Upon receipt of an application made in accordance with sub-Article (2) of this Article, the Ministry of Trade and Industry shall, after examining the matter in light of the relevant laws within two working days:

(a) register the share transfer or replace the business license upon receipt of the appropriate fee, where the application is found acceptable; or

(b) notify to the investor its decision and the reason thereof in writing, where the application is found unacceptable,"

6) Article 13 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Articles 13,14 and 15. Accordingly, Articles 14–38 of the Proclamation are renumbered as Articles 16–40, respectively.

"13. *Application for Investment Permit by a Domestic Investor*

1) An application for investment permit by a domestic investor shall be made in a form designed for such purpose and submitted together with the following documents:

(a) Where the application is signed by an agent, a photocopy of his power of attorney;

(b) Where the investment is to be made by an individual person, a photocopy of his identity card, or a photocopy of the certificate evidencing his domestic investor status and his recent two passport size photographs;

ሐ) ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው በንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ፎቶ ኮፒ ፣ ወይም ማኅበሩ አዲስ የሚቋቋም ከሆነ ከዚህ በተጨማሪ የማህበርተኞቹ የመታወቂያ ካርድ ፎቶ ኮፒ ወይም የሀገር ውስጥ ባለሀብትነት ሰርተፊኬት ፎቶ ኮፒ

መ) ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው በመንግሥት የልማት ድርጅት ከሆነ ድርጅቱ የተቋቋመበት ደንብ ፎቶ ኮፒ ወይም የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ፎቶ ኮፒ ፣ እና

ሠ) ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው በኅብረት ሥራ ማኅበር ከሆነ የማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ ፎቶ ኮፒ ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት የማመልከቻ ቅጽ እና ሠነዶች ፡

ሀ) ለኮሚሽኑ የሚቀርቡ ከሆነ በሁለት ቅጂ ፣ ወይም

ለ) ለክልል የኢንቨስትመንት አካላት የሚቀርቡ ከሆነ በአንድ ቅጂ ፣ መቅረብ አለባቸው ።''

''፲፬· <u>በውጭ ባለሀብት ስለሚቀርብ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ጥያቄ</u>

ማንኛውም የውጭ ባለሀብት አዲስ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማግኘት ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ከሚከተሉት ሠነዶች ጋር በሁለት ቅጂ ለኮሚሽኑ ማቅረብ አለበት ፡

ሀ) ማመልከቻው የተፈረመው በወኪል ከሆነ የውክልና ሥልጣን ማረጋገጫ ሠነድ ፎቶ ኮፒ ፣

ለ) ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው በግለሰብ ከሆነ የባለሀብቱን ማንነት የሚያሳዩ የፀና ፓስፖርት ገጾች ፎቶ ኮፒ እና ሁለት የቅርብ ጊዜ ጉርድ ፎቶግራፎች፣

ሐ) ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው ኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋመ የንግድ ማህበር ከሆነ የማህበሩ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ፎቶ ኮፒ ፣ ወይም ማህበሩ አዲስ የሚቋቋም ከሆነ ከዚህ በተጨማሪ የእያንዳንዱን የማህበሩን አባላት ማንነት የሚያሳይ የፀና ፓስፖርት ገጾች ፎቶ ኮፒ፣

መ) ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው ውጭ ሀገር በተቋቋመ የንግድ ማኅበር የኢትዮጵያ ቅርንጫፍ ከሆነ የማኅበሩ የመመስረቻ ጽሁፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ወይም የዚሁ ተመሳሳይ ሰነድ ፎቶ ኮፒ ፣ እና

ሠ) ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው በአገር ውስጥና በውጭ ባለሀብት ቅንጅት ከሆነ ከላይ በፊደል ተራ ''ሐ'' ከተገለጹት ሰነዶች በተጨማሪ እንደ አግባቡ የአገር ውስጥ ባለሀብቱ የመታወቂያ ካርድ ፎቶ ኮፒ ወይም የአገር ውስጥ ባለሀብትነት ሰርተፊኬት ፎቶ ኮፒ ።''

''፲፭· <u>ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል ስለሚቀርብ የኢንቨስትመንት ፈቃድ ጥያቄ</u>

፩) ማንኛውም ባለሀብት የማስፋፋት ወይም የማሻሻል የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለማግኘት ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ከሚከተሉት ሠነዶች ጋር ማቅረብ አለበት ፡

ሀ) የማመልከቻ ቅጹ የተፈረመው በወኪል ከሆነ የውክልና ሥልጣን ማረጋገጫ ሠነድ ፎቶ ኮፒ፣

ለ) ኢንቨስትመንቱ የሚካሄደው በንግድ ማኅበር ከሆነ የመመስረቻ ጽሁፍ እና የመተዳደሪያ ደንብ ፎቶ ኮፒ ፣ እና

ሐ) የነባር ድርጅቱ የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ ፎቶ ኮፒ ።

(c) Where the investment is to be made by a business organization, photocopies of its memorandum of association and Articles of association; or where the business organization is to be newly established, in additon, it shall submit photocopies of the shareholders' idntifty cards or photocopies of certificates evidencing there domestic investor status;

(d) Where the investment is to be made by a public enterprise, a photocopy of the Regulation under which it is established or a photocopy of its memorandum of association and Articles of association; and

(e) Where the investment is to be made by a cooperative society, a photocopy of its Articles of association.

2) The application form and documents stipulated under Sub-Article (1) of this Article shall be made:

(a) in two copies, where they are to be submitted to the Commission; or

(b) in one copy, where they are to be submitted to Regional Investment Organs''.

''14. *Application for Investment Permit by a foreign Investor*

Application for Investment Permit by a Foreign investor shall be made in a form designed for such purpose and submitted to the commission together with the following documents in two copies:

(a) where the application is signed by an agent, a photocopy of his power of attorney;

(b) where the investment is to be made by an individual person, a photocopy of the pages of a valid passport showing his identity and his recent two passport size photographs;

(c) where the investment is to be made by a business organization incorporated in Ethiopia, photocopies of its memorandum of association and Articles of association; or where it is to be newly established, in addition, it shall submit photocopies of the pages of a valid passport of each shareholder showing his identity;

(d) where the investment is to be made by a branch of a foreign business organization in Ethiopia, photocopies of its memborandum of association and Articles of association or a similar document of the parent company; and

(e) where it is a joint investment by domestic and foreign investors, in addition to the documents provided under (c) above, photocopies of identity cards or photocopies of certificates evidencing the domestic investor status of the domestic investors, as the case may be.''

''15 *Application for Investment Permit for Expansion or Upgrading*

1) An application for investment permit to expand or upgrade an existing enterprise shall be made in a form designed for such purpose and submitted together with the following documents:

a) where the application is signed by an agent, a photocompy of his power of attorney;

b) where the investment is made by a business organization, photocopies of its memorandum of association and Articles of association; and

c) photocopy of a valid business license of the existing enterprise.

፪) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት የማመልከቻ ቅጽ እና ሰነዶች ፡

ሀ) ለኮሚሽኑ የሚቀርቡ ከሆነ በሁለት ቅጂ ፡ ወይም

ለ) ለክልል ኢንቨስትመንት አካላት የሚቀርቡ ከሆነ በአንድ ቅጂ ፡ መቅረብ አለባቸው ።''

፯) የአዋጁ አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል ። እንዲሁም በአንቀጹ ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተጨምሮ ከንዑስ አንቀጽ (፪) እስከ (፭) ያሉት እንደ ቅደም ተከተላቸው ከ(፫) እስከ (፮) ሆነው ተሰተካክለዋል።

''፩· አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ማመልከቻው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ ፡ ፲፬ ወይም ፲፭ መሠረት ተሟልቶ ከቀረበለት በባለሀብቱ ሊካሄድ የተቃ ደውን የኢንቨስትመንት ሥራ ከዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም ከሚወጡ ደንቦችና መመሪ ያዎች አንፃር በመመርመር በአምስት የሥራ ቀናቶች ውስጥ ፡

ሀ) ማመልከቻውን ከተቀበለው ተገቢውን ክፍያ በማስከፈል ለባለሀብቱ የኢንቨስት መንት ፈቃድ ይሰጣል ፡ ወይም

ለ) ማመልከቻውን ካልተቀበለው ያልተቀበለ በትን ምክንያት ለባለሀብቱ በጽሁፍ ያሳውቃል ።

፪) አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት የኢንቨስትመንት ፈቃዱን ከሰጠ በኋላ ለአስፈ ላጊው ክትትል ለሚመለከታቸው የሴክተር መሥሪያ ቤቶች በደብዳቤ ያሳውቃል ።''

፰) በአዋጁ አንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሥር የሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ሠ) ተጨምሯል ።

''ሠ· ባለሀብቱ የንግድ ሥራ ፈቃድ ሳያወጣ በንግድ ሥራ ላይ ተሰማርቶ የተገኘ እንደሆነ ።''

፱) የአዋጁ አንቀጽ ፲፰ ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፳ ተተክቷል ።

''፳· <u>ስለ ቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት</u>

፩) ማንኛውም ባለሀብት ከኢንቨስትመንቱ ጋር በተያያዘ ሁኔታ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት በሚዋዋልበት ጊዜ ስምምነቱን ለኮሚሽኑ በማቅረብ ማስፈቀድና ማስመዝገብ አለበት ።

፪) ኮሚሽኑ ከላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የ ምዝገባ ማመልከቻ በቀረበለት በሁለት የሥራ ቀን ውስጥ የምዝገባ ማስረጃውን ለባለሀብቱ ይሰጣል ።

፫) በዚህ አንቀጽ መሠረት በኮሚሽኑ ያልተመዘገበ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነት ሕጋዊ ውጤት አይኖረውም።''

፲) የአዋጁ አንቀጽ ፷፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ለ) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ፊደል ተራ (ለ) ተተክቷል ።

''ለ) መደበኛ ነዋሪነቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ እንደአገር ውስጥ ባለሀብት በተቆጠረ የውጭ አገር ዜጋ የሚደረግ ኢንቨስትመንት''

፲፩) በአዋጁ አንቀጽ ፷፫ ሥር የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተጨምሮ የቀድሞው ንዑስ አንቀጽ (፪) እና (፫) እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ሆነዋል ። እንዲሁም የአንቀጹ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተሰርዟል ።

2) The application form and documents stipulated under Sub-Article (1) of this Article shall be made:

(a) in two copies, where they are to be submitted to the Commission; or

(b) in one copy, where they are to be submitted to Regional Investment Organs''.

7) Article 14 Sub-Article (1) of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (1). Besides, the following new Sub-Article (2) is added and Sub-Articles (2) up to (5) are renumbered as Sub-Articles (3) up to (6) respectively.

''1. Upon receipt of an application made in accordance with Articles 13, 14 or 15 of this Proclamation, the appropriate investment organ shall, after examining the intended investment activity in light of the Proclamation, Regulations and directives issued thereunder within five working days:

(a) issue the investment permit upon receipt of the appropriate fee, where the application is found acceptable; or

(b) notify to the investor its decision and the reason thereof in writing, where the application is found unacceptable.

2) The appropriate investment organ shall, after issuing the investment permit, notify the concerned government institutions so that the latter could conduct the necessary follow up''.

8) The following new item (e) is added under Article 16 Sub-Article (2) of the Proclamation.

''e. If the investor is found engaged in a commercial activity without obtaining a business license''.

9) Article 18 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 20.

''*20. Technology Transfer Agreement*

1) Where an investor concludes a technology transfer agreement related to his investment, he shall submit the same to the commission for approval and registration.

2) Upon receipt of an application for registration as per Sub-Article (1) of this Article, the Commission shall issue the registration certificate within two working days.

3) A technology transfer agreement which is not registered in accordance with this Article shall have no legal effect''.

10) Article 23 Sub-Article 1(b) of the Proclamation is deleted and replaced by the following new item (b)

''b. Investment made by a foreign national permanently residing in Ethiopia taken for a domestic investor''

11) The following new Sub-Article (2) is added under Article 23 of the Proclamation and the previous Sub-Articles (2) and (3) are renumbered as Sub-Articles (3) and (4) respectively. In addition, the previous Sub-Article (4) of this Article is deleted.

"፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ቢኖርም በአየር ትራንስፖርት አገልግሎትና በኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጨት ወይም ማስተላለፍ ወይም ማከፋፈል ሥራ ለሚሠማራ ባለሀብት የኢንቨስትመንት ፈቃድ የመስጠት ፣ የማደስና የመሰረዝ ሥራን እንደቅድም ተከተላቸው የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣንና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኤጀንሲ ኮሚሽኑን በመወከል ያከናውናሉ ።"

፲፪) የአዋጁ አንቀጽ ፳፬ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፬) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፬) ተተክተዋል ።

"፩. ኮሚሽኑ ወይም የክልል ኢንቨስትመንት አካላት የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለሰጡአቸው ባለሀብቶች አግባብ ባላቸው ህጎች መሠረት የሚከተሉትን አገልግሎቶች እንደ አግባቡ የሚመለከታቸውን የፌዴራል መንግሥት ወይም የክልል አስፈፃሚ አካላትን በመወከል ይሰጣሉ ፤

ሀ) የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ማዋዋል ፤

ለ) የንግድ ምዝገባ መፈፀም ፤

ሐ) ለውጭ ዜጋ ተቀጣሪዎች የሥራ ፈቃድ መስጠት ፤

መ) ለኮንስትራክሽን ሥራ ተቋራጮች ደረጃ መስጠት ፣ እና

ሠ) የንግድ ሥራ ፈቃድ መስጠት ።"

"፬) አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሠ) መሠረት የንግድ ሥራ ፈቃድ ማመልከቻ ሲቀርብለት ጉዳዩን አግባብ ካለው ሕግ አንፃር በመመርመር በአምስት የሥራ ቀን ውስጥ ፤

ሀ) ማመልከቻውን ከተቀበለው ተገቢውን ክፍያ በማስከፈል የንግድ ሥራ ፈቃዱን ይሰጣል ፤ ወይም

ለ) ማመልከቻውን ካልተቀበለው ያልተቀበለበትን ምክንያት ለባለሀብቱ በጽሁፍ ያሳውቃል ።"

፲፫) በአዋጁ አንቀጽ ፳፬ ሥር የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ፣ (፮) ፣ (፯) እና (፰) ተጨምረዋል ።

"፭) በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር ፶፯/፲፱፻፺፱ አንቀጽ ፳፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተው ቢኖርም አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት ባለሀብቱ አግባብነት ያላቸውን የአገሪቱን ሕጎችና መመሪያዎች ጠብቆ ለመሥራት ግዴታ እንዲገባ በማድረግ የንግድ ሥራ ፈቃድ ይሰጣል ።

፮) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ኮሚሽኑ የንግድ ሥራ ፈቃድ የሚሰጠው የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴርን በመወከል ብቻ ይሆናል ።

፯) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ከተጠቀሱት ሠነዶች ጋር በተያያዘ የሚደረጉ ማሻሻያዎችን የማዋዋል ፣ የማደስ ፣ የመተካት ወይም የመሠረዝ ሥራ የሚከናወነው አግባብ ባላቸው የፌዴራሉ መንግሥት ወይም የክልል አስፈፃሚ አካላት ነው ።

፰) አግባብ ያለው የኢንቨስትመንት መሥሪያ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱትን አገልግሎቶች ከሰጠ በኋላ ለአስፈላጊው ክትትል አግባብ ላለው የሴክተር መሥሪያ ቤት በደብዳቤ ያሳውቃል።"

"2. Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, the issuance, renewal and cancellation of investment permits for air transport services and for generation or transmission or supply of electrical energy shall be carried out by the Ethiopian Civil Aviation Authority and the Ethiopian Electric Agency respectively, representing the Commission".

12) Article 24 Sub-Articles (1) and (4) of the Proclamation are deleted and replaced by the following new Sub-Articles (1) and (4) respectively.

"1. The Commission or Regional Investment Organs shall provide the following services, as required under the relevant laws, to investors they have given investment permits, representing the competent Federal or Regional executive bodies, as appropriate:

(a) notarization of memorandum of association and Articles of association;

(b) effecting commercial registration;

(c) issuance of work permits to expatriate employees;

(d) grading of construction contractors; and

(e) issuance of business licenses".

"4. Upon receipt of an application for a business license in accordance with Sub-Article (1) (e) of this Article, the appropriate investment organ shall, after examing the matter in light of the relevant laws within five working days:

a) issue the business license upon receipt of the application fee, where the application is found acceptable; or

b) notify to the investor its decision and the reason thereof in writing, Where the application is found unacceptable".

13) The following new Sub-Articles (5), (6), (7) and (8) are added under Article 24 of the Proclamation.

"5. Notwithstanding the provision of Article 22 Sub–Article (2) (a) of Commercial Registration and Business Licensing Proclamation No. 67/1997, the appropriate investment organ shall issue the business license upon signing, by the investor, of an undertaking to respect the relevant laws and directives of the land.

6. Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, the Commission shall issue business licenses representing only the Ministry of Trade and Industry.

7. Notwithstanding the provision of Sub-Article (1) of this Article, amendments notarization, renewal, replacement or cancellation to be made in relation to documents stated therein shall be effected by the relevant Federal or Regional executive bodies.

8. The appropriate investment organ shall, after rendering the services listed under Sub-Article (1) of this Article, notify the concerned government institutions so that the later could conduct the necessary follow up".

፲፬) የአዋጁ አንቀጽ ፴ ተራ ቁጥር (፱) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ተራ ቁጥር (፱) ተተክቷል ።

"፱· ከኢንቨስትመንት ጋር የተያያዙ የቴክኖሎጂ ሽግግር ስምምነቶችን በመፍቀድ ይመዘግባል ፡"

፲፭) የአዋጁ አንቀጽ ፴፩ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፴፫፡ ተተክቷል ።

"፴፫፡ የኮሚሽኑ አቋም

ኮሚሽኑ ፡

ሀ) በመንግሥት የሚሾም ኮሚሽነር ፡ እና

ለ) አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል ።"

፲፮) የአዋጁ አንቀጽ ፴፯ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዞ በሚከ ተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል ።

"፪· እንደ አገር ውስጥ ባለሀብት መቆጠር የፈለገ መደበኛ ነዋሪነቱ ኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን የማመ ልከቻ ቅጽ በመሙላት ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር አያይዞ ለኮሚሽኑ ማቅረብ ይኖርበታል ፡

ሀ) ማመልከቻው የተፈረመው በወኪል ከሆነ የውክልና ሥልጣን ማረጋገጫ ሰነድ ፎቶ ኮፒ ፡

ለ) የፀና የንግድ ሥራ ፈቃድ ፎቶ ኮፒ ፡

ሐ) የዋና ምዝገባ የምስክር ወረቀት ፎቶ ኮፒ ፡

መ) የፀና የመኖሪያ ፈቃድ ፎቶ ኮፒ ፡

ሠ) የንግድ ሥራ ፈቃዱ የማኅበር ከሆነ የመመስረቻ ጽሁፍና የመተዳደሪያ ደንብ ፎቶ ኮፒ ፡

ረ) አመልካቹ እንደአገር ውስጥ ባለሀብት ለሚቆጠር መደበኛ ነዋሪነቱ ኢትዮጵያ ውስጥ የሆነ የውጭ አገር ዜጋ ጥገኛ ወይም ወራሽ ከሆነ አስጠጊው ወይም አውራሹ እንደአገር ውስጥ ባለሀብት የሚቆጠር ስለመሆኑ ከላይ ከተጠቀሱት ሰነዶች በተጨማሪ የጥገኛው የፀና የመኖሪያ ፈቃድ ፎቶ ኮፒ ፡ ወይም አመልካቹ ወራሽ ለመሆኑ በፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ ፎቶ ኮፒ ፡

ሰ) የአመልካቹ ሦስት የቅርብ ጊዜ ጉርድ ፎቶግ ራፎች።"

፲፯) በአዋጁ የሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፵፩ ተጨምሮ ከ፵፩– ፵፪ ያሉት የአዋጁ አንቀጾች እንደቅደም ተከተላቸው ከአንቀጽ ፵፪–፵፭ ሆነው ተስተካክለዋል ።

"፵፩· ለኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣንና ለኢ ትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኤጀንሲ ስለተሰጠ ውክልና

የኢትዮጵያ ሲቪል አቪዬሽን ባለሥልጣንና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኤጀንሲ ፡

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በውክልና የተሰጣቸውን ተግባር የሚያከ ናውኑት በዚህ አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት ይሆናል።

ለ) በተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን መሠረት የሰጧ ቸውን የኢንቨስትመንት ፈቃድ ኮፒ እና አግባብ ያላቸውን ሰነዶች ፎቶ ኮፒ ለኮሚሽኑ ያስተላ ልፋሉ።"

14) Article 30 item number (9) of the Proclamation is deleted and replaced by the following new item number (9).

"9. approve and register technology transfer agreements related to investments;"

15) Article 31 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 33.

"33. Organization of the Commission

The Commission shall have:

(a) a Commissioner to be appointed by the Government; and

(b) the necessary staff."

16) Article 37 Sub-Article (2) of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (2)

"2. A foreign national permanently residing in Ethiopia to be taken for a domestic investor shall fill a form designed for such purpose and submitted together with the following documents to the commission:

(a) where the application is signed by an agent, his power of attorney;

(b) a photocopy of valid business license;

(c) a photocopy of principal registration certificate;

(d) a photocopy of valid residence permit;

(e) where the business license is that of a business organization, photocopies of its memorandum of association and Articles of association;

(f) where the applicant is dependent or heir of a person taken for a domestic investor and permnantly residing in Ethiopia, in addition to the above mentioned documents pertaining to the supporting person or the deceased, a photocopy of the dependent's valid residence permit or a court decision declaring his status as an heir; and

g) the applicant recent three passport size photographs".

17) The following new Article 41 is added. Accordingly, Articles 39-42 of the Proclamation are renumbered as Articles 42-45, respectively.

"41. Power Delegated to the Ethiopian Civil Aviation Authority and the Ethiopian Electric Agency.

The Ethiopian Civil Aviation Authority and the Ethiopian Electric Agency shall:

(a) carry out functions delegated to them under Article 25 Sub–Article (2) in compliance with this Proclamation and Regulations and Directives issued thereunder.

(b) forward to the Commission photocopies of the investment permits they issued and the relevant documents".

፬. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፫ ፣ ፲፬ ፣ ፲፭ እና ፴፯ የተጠቀሱትን ሰነዶች ዝርዝር የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ሊያሻሽል ይችላል ።

5. *Power to Issue Regulations*

The Council of Ministers may issue Regulations to amend the list documents stipulated under Articles 13, 14, 15 and 37 of this Proclamation.

፭. የተሻረ ሕግ

የቴክኖሎጂ ሽግግር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፳፩/፲፱፻፺፫ በዚህ አዋጅ ተሽሯል ።

5. *Repealed Law*

Transfer of Technology Council of Ministers Regulation No. 121/1993 is hereby repealed.

፮. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከጥቅምት ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

6. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 28th day of October, 2003.

አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፯ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ.ም

Done at Addis Ababa, this 28th day of October, 2003.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳንት

GIRMA WOLDEGIORGIS

PRESIDENT OF THE FEDERAL

DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA